እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ ተመለሱ (ተውበት አድርጉ)፤ እኔ በቀን መቶ ጊዜ ወደርሱ እመለሳለሁ (ተውበት አደርጋለሁ።)

ከአልአገርሪ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን)
ሶሐቦች መካከል አንዱ ነበር። እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ ተመለሱ (ተውበት አድርጉ)፤ እኔ በቀን መቶ ጊዜ ወደርሱ እመለሳለሁ (ተውበት አደርጋለሁ።)"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሰዎች ተውበትና ምህረት መጠየቅን እንዲያበዙ አዘዙ። እርሳቸው የቀደመውም ሆነ የወደፊት ወንጀላቸው የተማረ ከመሆኑም ጋር እሳቸውም በቀን ከመቶ ጊዜ በላይ ወደ አላህ ተውበት እንደሚያደርጉና ምህረት እንደሚጠይቁ ተናገሩ። ይህም ለአላህ ያላቸውን የተሟላ መዋደቅና የተሟላ ባርነትን የሚያሳይ ነው።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/4809